## የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ

## የሞት ማስረጃ የሌለው ሟች

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ ሚያዝያ 27 ቀን 1950 ዓ/ም ተከፍቶ ሐምሌ 28 ቀን 1969 ዓ/ም ተዘግቷል። በነዚህ 19 ዓመታት ውስጥ በተሠለፉበት የሥራ መስክ አንቱ የተባሉ ሞያተኞችን ያፈራው ዝነኛው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ ለምንና በማን ትዕዛዝ እንደተዘጋ የጽሁፍ ማስረጃ አላገኘሁም። አንድ ሰው ሲሞት፤ ለመሞቱ ማረጋገ ጫ ሠርተፊኬት ይሰጣል። በተመሳሳይ አንድ ትልቅ ተቋምም ሲዘጋ በጽሑፍ ትዕዛዝ ይሆናል፤ ሕጋዊነቱን ለማረጋገጥ ማለት ነው፤ ይህ ባልተሟላበት ከሆነ የተዘጋው ብዙ ጥያቄዎችንና መላምቶችን ያስከትላል። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚም አዘጋግ እንቆቅልሽ ሆኖ ቆይቷል አሁንም ነው። በሕዝብ ዘንድ የሚታወቅ አይደለም፤ ከአካዳሚው የተመረቁትም በጥቅሉ በሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማሪያም በጥላቻ ተዘጋ እንጂ ዝርዝሩን የሚያውቁት አይመስለኝም ። ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ አካዳሚውን ለምን ጠሉት? አዘጋጉን እንቆቅልሽ የሚያደርገው የእሳቸው ጥላቻ መንስኤ አለመታወቁ ነው። እኔም ለማወቅ በነበረኝ ጉጉት ከለቃቅምኳቸው የተገነዘብኩት በአጭሩ የሚከተለው ነው።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ ንጉሡ ለሀገር ዕድገትና ደህንነት መሠረት ይሆናሉ ብለው ከመሠረቷቸው እንደ ከፍተኛ የትምህርት ማዕከሎች፤ ባንክ፤ አየር መንገድ፤ መብራት ኃይል፤ ቴሌኮሚኒኬሽን የመሳሰሉት ተቋማት አንዱ ነው። ንጉሠ ነገሥቱ በማይጨው ጦርነት የተሸነፉት በሠራዊት ቁጥር ማነስ ወይም በወኔ ማጣት ሳይሆን በጊዜው ቴክኖሎጂ ያፈራውን ዘመናዊ መሣሪያ በታጠቀ፤ በተማረና በሰለጠነ ሠራዊት ስለሆነ የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ የተማረ ሠራዊት አስፈላጊነትን ገና በጧቱ ተገንዝበዋል። በዚህም መሠረት ቀደም ሲል የተቋቋሙት የክብር ዘበኛ ዕጩ መኮንኖች ማሰልጠኛ ት/ቤት ሦስት ኮርሶችን ካስመረቀ በኋላ የተቋቋመበትን ዓላማ አከናውኖ በ1940ዎቹ መጨረሻ ቢዘጋም የሆሎታ ገነት ጦር ት/ቤት ግን መኮንኖችን ማስመረቁን ቀጥሏል፣ ሆኖም ብዙዎቹ መኮንኖች በወታደርነት ካገለገሉ በኋላ መኮንን ስለሚሆኑ በዕድሜ መግፋት የተነሣ ረጂም ግልጋሎት ስለማይሰጡ እንደ ምዕራባውያን ሀገሮች ሁሉ የላቀ የትምህርት ደረጃ ያላቸውን ወጣቶች ከትምህርት ቤት መልምሎ በወታደራዊ ሳይንስና በቀለም ትምህርት ማሰልጠኑ ለረጅም ጊዜ ግልጋሎትና ለከፍተኛ ኃላፊነት አስፈላጊ ነበር። ከዚህም ሌላ ሀገሪቱ በምትሳተፍባቸው የዓለም አቀፍ ተልዕኮ ከሌሎች ሀገሮች መኮንኖች ጋር ተግባብቶ ለመሥራት የሚያስችል መሆኑም በጽኑ ታምኖበት አካዳሚውን የማቋቋሙ አስፈላጊነት አማራጭ አልነበረውም።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚን ለማቋቋም ሃሳቡ ሲጠነሰስ ጀምሮ የገጠመው ተቃውሞ አብሮት አድጎ ለመቃብር አብቅቶታል። አካዳሚውን ለማቋቋም ሲታሰብ በሀገር መከላከያ ውስጥ የነበሩት ከፍተኛ ባለሥልጣናት የመከላከያ ሚኒስትሩ ሌተና ጄኔራል አበበ አረጋይ (ብዙ ጊዜ የሚጠሩት ራስ አበበ አረጋይ በሚለው ስያሜ ነው)እና የጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹም ሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ነበሩ። ሁለቱ ባለሥልጣናት ስለአካዳሚው ምስረታ የነበራቸው አስተሳሰብና አመለካከት የተለያየ ነበረ። ልዩነቱንም የፈጠረው ወደሥልጣን በመጡበት ጎዳና ላይ የቀሰሙት ልምድ እንደነበረ ይታሰባል።

ራስ አበበ አረጋይ የጠለቀ የአካዳሚክም ሆነ የወታደራዊ ትምህርት ሳይኖራቸው ተፈጥሮ ባደለቻቸው የመሪነት ችሎታ ለያዙት ቦታና ማዕረግ በቅተዋል። በዚህ ጉዟቸው ላይ ውጪ አገር ሄደው የዘመኑን የጦር አካዳሚዎችን የመጎብኘት ዕድል ባለማግኘታቸው ለሀገራችን የአካዳሚን አስፈላጊነት የተገነዘቡ አልነበሩም። የውጪ ወታደራዊ አማካሪዎች እንደነበሯቸው ይታመናል፤ ስለዘመናዊ የጦር አካዳሚ አስፈላጊነት ሃሳብ ሳያነሱባቸው አይቀርም ሆኖም በነበራቸው የራስ መተማመን ጠንካራ መንፈስ የማያምኑበትን በቀላሉ በአማካሪዎች ግፊት የማይቀበሉ እንደነበሩ ይነገርላቸዋል።

ራስ አበበ አረጋይ ንጉሡ ወደ ሥልጣን ከተመለሱ ጀምሮ ለአንድ ዓመት ብቻ የሲዳሞ ገዢ ከመሆናቸው በስተቀር እስከ 1953 ዓ/ም ድረስ የጦር ሚኒስትር ቀጥሎም መከላከያ በአዲስ መልክ ሲደራጅ የመከላከያ ሚኒስትር ሆነው የሠሩ ናቸው። የጦር ሚኒስቴር ተብሎ የሚታወቀው የምድር ጦር፤ የክብር ዘበኛና የፀጥታ ተብለው የሚታወቁ ክፍሎችን ያካተተ ነበር። ለነዚህ ክፍል መኮንኖች የሚከፈለው ደመወዝ ወጥ አልነበረም። ለአንዱ ክፍል ም/መቶ አለቃ 93 ብር ሲከፈል፤ ለሌላው ክፍል ሻምበል 60 ብር ይከፈል ነበር። ይህ ሁኔታ በንጉሡ ተፈቅዶ የሚሰራበት ስለነበር ራስ አበበ ሊያስተካክሉት ያልቻሉ ከፍተኛ ራስ ምታት ሆኗቸው የቆየ ነበር። ራስ አበበ ለአንድ ዓይነት ማዕረግ አንድ ዓይነት ክፍያ ማድረጉ ተገቢና ፍትሐዊ ነው ብለው የሚያምኑ ነበሩ።

ራስ አበበ ከላይ እንደተገለጠው የጦር ሚኒስትር በነበሩበት ጊዜ የነበረው የደሞወዝ ልዩነት በአስተዳደር በኩል ከፍተኛ ችግር ገጥሟቸው ስለነበር፤ አሁንም አዲስ በተደራጀው መከላከያ አካዳሚው ተቋቁሞ የሚመረቁት መኮንኖች የደመወዝ ክፍያ ከሆሎታና ከክቡር ዘበኛ ምሩቆች የተለየ እንደሚሆን በመገመት ይህ ደግሞ ያሳለፉትን ዓይነት የአስተዳደር ችግር እንደሚያስከትል በመገንዘባቸው የአካዳሚውን መቋቋም የሚደግፉ አልነበሩም። የፈሩትም አልቀረ የሳቸውና የሌሎችን ሕይወት ለቀጠፈው የ1953ቱ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ የደመወዝ ልዩነቱ ዋና ምክንያት ባይሆንም የክብር ዘበኛ መኮንኖችን ለአመጽ ለማነሳሳት መቀስቀሻ መሣሪያ ሆኖ አገልግሏል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከእሳቸው ጋር የመጀመሪያው የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም ሆነው የተሾሙት ሜ/ጀኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ክብር ዘበኛን አዛዥ ሆነው በስዊድን አማካሪዎች እየተረዱ በአዲስ መልክ ሲያደራጁ፤ 3 ተከታታይ ኮርስ የክብር ዘበኛ ዕጩ መኮንኖችን በስዊዲኖች አስተማሪነት ሲያስመርቁና 4 ዙር የኮሪያ ዘማች ሻለቆች በአሜሪካኖች አማካሪነት ሲያደራጁ ባካበቱት ልምድና የሀገሪቱን የመከላከያ ብቃት ለማሳደግ ከነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ የአካዳሚውን መመሥረት ከሚደግፉት ውስጥ በግንባር ቀደም የሚጠቀሱ ነበሩ።

ንጉሡ ከሕንድ መሪ በተደረገላቸው የክብር ጥሪ መሠረት የመጀመሪያ ጉብኝት ለማድረግ በ1949 ዓ/ም ሕንድ ገብተው የቅርብ ወዳጃቸው በሆኑት የሕንዱ መሪ ኔህሩ አማካኝነት ከጎበኟቸው ተቋማት ውስጥ አንዱ የሕንድ ብሔራዊ የመከላከያ አካዳሚ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ በአዩትና በተደረገላቸው ገለጻ ተደስተው በተመሳሳይ ደረጃ የሆነ የጦር አካዳሚ በሕንዶች እንዲቋቋም ፈልገው በወቅቱ በሕንድ የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበሩትን ራስ እምሩ ኃይለሥላሴን ሃሳብ ጠየቁ። አምባሳደሩም ቀደም ሲል ጀምሮ ንጉሡ የጦር አካዳሚ

ለማቋቋም የነበራቸውን ፍላጎት ስለሚያውቁ እሳቸውም ጉዳዩን በቅርብ የሚያውቁትና የሚከታተሉት ስለበር ያለምንም ማቅማማት የንጉሡን ሃሳብ በመደገፍ የሕንድ ብሔራዊ አካዳሚ በእንግሊዞች የተቋቋመና ከእንግሊዝ፤ ፈረንሳይና አሜሪካ የጦር አካዳሚዎች ያልተናነሰ ደረጃ ያለው በመሆኑ የኢትዮጵያንም ሕንዶች ቢያቋቁሙት ተመሳሳይ ደረጃ ይኖረዋል፤ በወጪም አኳያ ከሀገሪቱ አቅም ጋራ የተጣጣመ ይሆናል በማለት ስለመከሯቸው የመከላከያ ባለሥልጣኖቻቸውን ሳያማክሩ አካዳሚው በሕንዶች እንዲቋቋም ወስነው ከሕንድ መንግሥት ጋር ስምምነት ፈርመው ተመለሱ። ጉዳዩ ኤታማዦር ሹሙን ሲያስደስት ራስ አበበን ቅር ቢያሰኝም የንጉሡ ውሳኔ በመሆኑ ሊለውጡት የሚችሉት ነገር አልነበረም።

አካዳሚውን እንዲያቋቁሙ ከሕንድ የተላኩት ጄኔራል ራውሊ በመጀመሪያ የተሰጣቸው ግዳጅ አካዳሚውን በጥሩ መሠረት ላይ ማቋቋም ሲሆን ቀጥሎም የአካዳሚው አዛዥ ሆነው ከትምህርት ቤት ተማሪዎችን መልምለው ከፍተኛ የሆነ ወታደራዊ ሥልጠናና የአካዳሚክ ትምህርት ሰጥተው ብቃትና ጥራት ያላቸው መኮንኖች እንዲሆኑ አድርጎ ማስመረቅ ብቻ ነበር። አካዳሚው በአቋም በመከላከያ ሥር የነበረ ቢሆንም በአፈጻጸምና በተግባር ግን በቀጥታ በንጉሡ ሥር ስለነበር የአካዳሚው አዛዥ ማንኛውንም ጉዳይ አቅርቦ የሚያስፈጽመው ቀጥታ ንጉሡ ዘንድ ነበር።

ለ1ኛ ኮርስ በወቅቱ ከነበሩት ሦስት ኮሌጆች ውስጥ ከፍተኛ ውጤት የነበራቸውን የ1ኛ ዓመት ተማሪዎችን በንጉሡ አስመልማይነት በግድ የተመረጡ ተማሪዎች አካዳሚ ከመግባታቸው በፊት መመሪያ ለመቀበል በቤተ መንግሥት ግርማዊ ጃኖሆይ ፊት ቀርበው ነበር፤ ንጉሡም አካዳሚ ገብቶ መመረቅ ምን ያህል ክብር እንደሚያጎናጽፍና ወደፊትም ሠራዊቱ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ዕድገት ካሳወቋቸው በኋላ "ሥልጠናችሁ ጨርሳችሁ በምትመረቁበት ጊዜ ከጓደኞቻችሁ አናሳንሳችሁም" የሚል የተስፋ ቃል ሰጥተው አሰናበቷቸው። እዚህ ጋ ንጉሡ አንድ ማሠሪያ ማበጀት ነበረባቸው፤ ሊከፈላቸው ይገባል ብለው ያሰቡትን በአዋጅ ቢያስነግሩ ኖሮ የሆሎታና የክ/ዘበኛ ምሩቅ መኮንኖችን ታቃውሞ ሊያስቀር ይችል ነበር ተብሎ ይታሰባል።

የ1ኛ ኮርስ ዕጩ መኮንኖች የ3 ዓመት ሥልጠና ጨርሰው በምክትል መቶ አለቃ ማዕረግ እስከተመረቁ ድረስ የደመወዝ ጉዳይ በምስጢር ተይዞ የቆየ ነበር። ከላይ እንደተጠቀሰው የአካዳሚው አዛዥ ከንጉሡ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ስላላቸው ከምረቃው ቀደም ብሎ ለአካዳሚ ምሩቆች ከነሱ በፊት ለም/መ/አለቃ በተመደበው ደመወዝ ላይ ዘጠና ብር የችሎታ ላቂያ በአበል መልክ ሳይሆን በቋሚነት እንዲከፈላቸው አዛዡ ሃሳብ አቅርበው ተቀባይነት ሊያገኝ ችሏል። በምረቃው ቀን አካዳሚው ለተመራቂዎችና ለክብር ዕንግዶች ባደረገው የምረቃ ግብዣ ላይ የአካዳሚው አዛዥ ብ/ጄኔራል ራውሊ ለተመራቂዎች የወር ደመወዛቸው ብር 215.00 (መደበኛ ደመወዝ 125.00 የድፕሎማ 90.00) መሆኑን አሳወቁ።

በምዕራቡ ዓለም ሠራዊት ለየማዕረጉ አንድ ወጥ የሆነ የደሞዝ ሠንጠረዥ አለ፤ ማንኛውም መኮንን የተመረቀበት ተቋምና ያለውም ድግሪ ግምት ሳይገባ የሚከፈለው በያዘው ማዕረግ የደሞዝ ሊስት መሠረት ብቻ ነው፤ የተመረቀበት ተቋም ወይም ያለው ድግሪ ለወደፊት ዕድገቱ መወጣጫ መሰላል ነው። ጄኔራል ራውሊ ለድፕሎማም ሆነ ለድግሪ የተለየ ክፍያ እንደማይደረግ ጠንቅቀው ያውቃሉ፤ ራሳቸው መጠየቅ ቀርቶ ንጉሡ እንኳን እንዲከፈል ቢያዙ ከራሳቸው ሀገር ሠራዊት ልምድ ተነስተው ትክክል አለመሆኑን ለንጉሡ ማስረዳት

ይጠበቅባቸው ነበር። ጀኔራል ራውሊ አካዳሚውን በጥሩ መሠረት ላይ ያቋቋሙ በመሆኑ “የአካዳሚው መሥራች አባት” የሚል ስም የሚያሰጣቸው ቢሆንም ለአካዳሚ ምሩቆች የ90 ብር ጭማሪ እንዲደረግ ንጉሡን ማስፈቀዳቸው ግን ጊዜውን ጠብቆ አካዳሚውን የሚያፈርስ 90 ፓውንድ ፈንጂ ቀብረው ነው የሔዱት። የተቀበረውም ፈንጂ ጊዜውን ጠብቆ ፈንድቶ አካዳሚውን አፍርሷል።

የ90 ብር የድፕሎማ አበል ጭማሪ እንደተፈራው በሁለት አቅጣጫ የአልተጠበቀ ቅራኔ ፈጠረ። ባንድ በኩል ከአካዳሚ የተመረቁ መኮንኖች ከእኛ የተለየ ምን የሚሠሩት አለና ነው 90 ብር የሚጨመርላቸው፤ እኩል ሊከፈለን ይገባል የሚል ከሆሎታና ከክ/ዘበኛ ጦር ት/ቤቶች በተመረቁ መኮንኖች ዘንድ ጥያቄ አስነሳ።

በሌላ በኩል ደግሞ የአካዳሚ ምሩቃኑም ጭማሪውን በቂ ነው ብለው አልተቀበሉትም። ንጉሡ አካዳሚውን ሲከፍቱ፤ በግድ ከኮሌጅ ለተመለመሉ ዕጩ መኮንኖች፤ ከኮሌጅ ከሚመረቁ ጓደኞቻችሁ አናሳንሳችሁም ብለው የገቡት ቃል ባለመጠበቁ ቅሬታ አሳድሮ፤ አቤቱታም አስከተለ። በወቅቱ ለኮሌጅ ምሩቅ የሚከፈለው 450 ብር ስለነበር የአካዳሚው ምሩቃኑም በዚሁ ደረጃ እንዲከፈላቸው አቤቱታና ትግል ጀመሩ። የተገባልን ቃል አልተጠበቀም በሚል የ2ኛ፣3ኛና 4ኛ ኮርስ ዕጩ መኮንኖች አቤቱታ አቀረቡ ገና ከጅምሩ አካዳሚውን በበጎ ዓይን የማይመለከቱት የመከላከያ ባለሥልጣናት አቤቱታውንና ትግሉን ለማፈን በወቅቱ ሥልጠና ላይ የነበሩ ዕጩ መኮንኖችን በአጠቃላይ ሲቀጡ መሪ ናቸው ባሏቸው ግለሰቦች ላይ ደግሞ ከባድ እርምጃዎች ወስደዋል፤ ሆኖም የአካዳሚው ምሩቃን ጥረት በአዲስ አበባ ቀጥሎ አቤቱታው ንጉሡ ዘንድ ለመድረስ በቅቷል። ንጉሡም የተወካዮቹን አቤቱታ ከአዳመጡ በኋላ እርምጃ እንደሚወሰድ ቃል ገብተው አሰናበቷቸው።

በሆሎታም ሆነ በአካዳሚ ምሩቃን ዘንድ ያሉትን ቅሬታዎች ይፈታል ተብሎ ተጠንቶ በ1961 ዓ/ም የተወሰደው እርምጃ ፤ 90 ብር የትምህርት አበል እንዲቀርና ለሁሉም መኮንኖች የደሞዝ ጭማሪ ተደርጎ አንድ ዓይነት ሆኗል። ይህ ድርጊት የአካዳሚ ምሩቃን የሚፈልጉት ግብ ላይ ያላደረሰ ቢሆንም ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር ስለሌለ ቅሬታቸውን ይዘው እንዳሉ ሌላ ሁኔታ ተከሰተ።

1ኛ ኮርስ አካዳሚ ሚያዝያ 27 ቀን 1950 ዓ/ም ገብተው መስከረም 21 ቀን 1953 ዓ/ም ተመረቁ። 1ኛ ኮርስ በትምህርት ላይ እያሉ 19ኛ ኮርስ ሆሎታ ገነት ጦር ት/ቤት መስከረም 1951 ዓ/ም ገብተው ቀድመው ሚያዝያ 1952 ዓ/ም በመመረቃቸው ቀደምት ወይም ሲኒዬር ሊሆኑ በቅተዋል። እስከ ሻምበል ማዕረግ ድረስ የ19ኛ ኮርስ መኮንኖች በቅድሚያ እየተሾሙ የማዕረግ ቀደምትነቱን (ሲኒዬሪቲ) ይዘው ቆይተዋል።በሻለቅነት ማዕረግ ላይ ግን የአካዳሚ 1ኛ ኮርስ መኮንኖች ከማዕረግ መቆያ ጊዜያቸው አንድ ዓመት ቀድመው ተሹመው የ19ኛ ኮርስ ሲኒዬር ለመሆን በቁ። ይህ ድርጊት አካዳሚዎች ንጉሡ ቃላቸውን አልጠበቁም የሚለውን ቅሬታ ለመፍታት የተደረገ ሲመስል በሌላ በኩል ደግሞ የአልተጠበቀ ችግር አስከተለ።

በ90 ብር ጭማሪ የተነሣ ከሆሎታና ከክ/ዘበኛ ማሠልጠኛ ተቋማት የተመረቁ መኮንኖች ዘንድ የነበረውን ቅሬታ የደመወዙ መስተካከል ያስቀረዋል ተብሎ ነበር፤ ሆኖም እኛ አምስት ዓመት ስንጠብቅ አካዳሚዎች በአራት ዓመት ተሾሙ በማለት የነበረው ቅሬታ እንደገና አገረሸ። የሆሎታ 19ኛ ኮርስ መኮንኖች ግንባር ቀደም በመሆን ለምን ቀድመን አልተሾምንም የሚል

ጥያቄ አነሱ። በምስራቅ 3ኛ ክ/ጦርና በሰሜን 2ኛ ክ/ጦር ውስጥ ስውር እንቅስቃሴዎች ተጀመሩ። ዕንቅስቃሴው ማዕረግ ይሰጠን በማለት በቀጥታ አቤቱታ ላይ ያተኮረ ሳይሆን በአካዳሚውና በአካዳሚው ምሩቆች ላይ ያነጣጠረ ነበር። አካዳሚዎች ለሀገራቸው ደም ሳይሆን ወተት ያፈሳሉ፤ እኛ የእንጀራ ልጅ አካዳሚዎች የቤት ልጅ የመሳሰሉ ቅስቀሳዎችን የያዙ ጽሑፎች በስውር ይበተኑ ነበር። በ3ኛ ክ/ጦር የዕንቅስቃሴው አስተባባሪና መሪ የ19ኛ ኮርስ አባል፤ በወቅቱ ሻምበል፤ መንግሥቱ ኃ/ማሪያም ነበሩ።

አዲስ ክፍል ሲቋቋም በአሮጌው አለመወደድ አያስገርምም፤ እናም ቀደም ሲል ከነበሩት የመኮንኖች ማሠልጠኛ ተቋማት የተመረቁ ጥቂት መኮንኖች ለአካዳሚው በጎ አመለካከት እንዳልነበራቸው ቢገመትም የሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ግን የተለየ ነበር። ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ በአካዳሚው ላይ ጥላቻ ያደረባቸው ከሆሎታ ተመርቀው ሐረር 3ኛ ክ/ጦር መሣሪያ ግ/ቤት ከተመደቡ ጊዜ ጀምሮ ነበር፤ ምክንያቱን እሳቸውና እሳቸው ብቻ ናቸው የሚያውቁት። የጦር አካዳሚው በየዓመቱ ዕ/መኮንኖችን ሲያስመርቅ የክ/ጦሩ ልዩ ልዩ ክፍል አዛዦች በበዓሉ ላይ እንዲገኙ ይጋበዛሉ። ሌ/ኮ መንግሥቱ የመሣሪያ ግ/ቤት አዛዥ ከመሆናቸው በፊትና አዛዥ በነበሩም ጊዜ ልዩ ልዩ ምክንያት በመስጠት በምረቃው በዓል ላይ አንድም ጊዜ ተገኝተው አያውቁም። በ3ኛ ክ/ጦርና በአካዳሚው መኮንኖች ክበቦች ውስጥ በበዓላት ቀን አንድ ጊዜ 3ኛ ክ/ጦር ሌላ ጊዜ በአካዳሚው የቢንጎ ጫወታ ይካሄዳል። ታዲያ የ3ኛ ክ/ጦር መኮንኖች ወደ አካዳሚው፤ የአካዳሚው መኮንኖች ወደ ክ/ጦሩ ክበብ እየሄዱ መጫወት የተለመደ ነበር። ሌ/ኮ መንግሥቱ በክ/ጦሩ ክበብ እየተገኙ ይጫወታሉ፤ ግን በአካዳሚው ክበብ ውስጥ አንድም ጊዜ ገብተው ተጫውተው አያውቁም። በአካዳሚው በሚደረጉ ዕንቅስቃሴዎች አለመሳተፋቸው የጥላቻቸው መግለጫ ሲሆን መነሻው ምን እንደሆነ ለማወቅ የሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ ማሪያምን አስተዳደግና የኋላ ታሪክ ምርምር የሚጠይቅ ይሆናል።

አካዳሚው በራሱ ጋራዥ የተሽከርካሪዎች ጥገና ቢያደርግም አንዳንድ ከበድ ያሉ ሥራዎች ሲገጥሙ በክ/ጦሩ መሣሪያ ግ/ቤት ይረዳ ነበር። ጀኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ የአካዳሚው አዛዥ በነበሩበት ጊዜ የጀምስ መኪና ሞተር ተበላሽቶ መለወጥ ነበረበትና በወቅቱ የመሣሪያ ግ/ቤት አዛዥ ለነበሩት ለሻምበል መንግሥቱ በመደወል ዕርዳታ ይጠይቃሉ። መሣሪያ/ግ/ቤት የተቋቋመው የአካዳሚውን ሥራ ለመሥራት አይደለም፤ በአካዳሚውም አይታዘዝም የሚል መልስ ከሻምበሉ ያገኛሉ። ሁኔታው ቅር ቢያሰኛቸውም ጉዳያቸውን ለማስፈጸም በክ/ጦሩ አዛዥ በጀኔራል አበበ ገመዳ በኩል ትዕዛዙ ለሻምበል መንግሥቱ እንዲደርስ ያደርጋሉ፤ አሁንም ሻምበሉ ሥራውን እያጓተተ እንዳበሳጫቸውና ለሁለቱ ሰዎች ቅራኔ መነሻ መሆኑ በወቅቱ መሣሪያ/ግ/ቤት ይሠሩ የነበሩ የአካዳሚ ምሩቆች ይናገራሉ።

ይህ በዚህ እንዳለ ሻምበል መንግሥቱ በሥራቸው ጉብዝና የክ/ጦሩ አዛዥ ጀኔራል አበበ ገመዳ ይወዷቸው ስለነበር ለትምህርት ወደ አሜሪካ ለሁለተኛ ጊዜ ልከዋቸው እዚያ እንዳሉ ፤ ጀኔራል አበበ ገመዳ የክ/ዘበኛ አዛዥ፤ ጀኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ ደግሞ የ3ኛ ክ/ጦር አዛዥ ሆነው ይሾማሉ። ሻምበል መንግሥቱ ከአሜሪካ ተመልሰው አዲስ አበባ ሲደርሱ ሁኔታውን ይሰሙና ጀኔራል አበበን ወደ እሳቸው ጋ እንዲያስቀይሯቸው ያመለክታሉ። ጀኔራሉም የምድር ጦር አዛዥን ይጠይቃሉ፤ ምድር ጦር በበኩሉ የጀኔራል ኃይሌን ይሁንታ ይጠይቃል። በዚህ ጊዜ የ10ኛ ሜ/ብርጌድ ጂጂጋ ላይ አዲስ ከአሜሪካ የመጡ መሣሪያዎች በመታጠቅ ላይ ስለነበር በተማሩት ሞያ እንዲሰሩ የብርጌዱ ድርጅት መኮንን አድርጌ የመደብኩኳቸው ስለሆነ

አልስማማም ይላሉ ጀኔራል ኃይሌ ። ሻምበል መንግሥቱ ሐረር ተመድበው በማታ የአካዳሚክ ትምህርት እንዲማሩ ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ጂጂጋ ሥራ ጀመሩ፤ ሆኖም ዝውውር የተከለከልኩትና ከመሣሪያ/ግ/ቤት የተዛወርኩት ለብቀላ ነው በማለት በጀኔራል ኃይሌ ላይ ቂም ቋጠሩ።

ሁኔታው በዚህ መልክ እያለ የ1ኛ ኮርስ ቀድሞ የመሾም ጉዳይ መጣና ሻምበል መንግሥቱ ለአቤቱታ ጀኔራል ኃይሌ ዘንድ ቀረቡ። ምንድነው ጉዳይህ ተብለው ሲጠየቁ፤ የበታቾቼ ሲሾሙ እኔ ለምን አልተሾምኩም ብለው ይጠይቃሉ። ጄኔራሉም የበታቾቹ ከምትላቸው አንድ ሰው ጥራልኝ ይላሉ። ሻምበል መንግሥቱ የሻለቃ ጥበበ መንክርን ስም ይጠቅሳሉ። (ሻለቃ ጥበበ መንክር ከአካዳሚ 1ኛ ኮርስ 1ኛ የወጡ ሲሆን በወታደራዊና በአካዳሚክ ትምህርቶች የአስመዘገቡት ከፍተኛ ውጤት ላይ ማንም እንዳልደረሰበት ይወሣል) ጀኔራል ኃይሌ ስለ ሹመቱና ስለተጠቀሰው ሻለቃ ለማስረዳት ሲሞክሩ አለመግባባት ተፈጥሮ ሻምበሉ ከቢሯቸው በወታደር ፖሊስ እንዲወጡ ተደርጓል።

የሻምበል መንግሥቱ ሥውር ዕንቅስቃሴ አዲስ በተቋቋመው 10ኛ ሜ/ብርጌድ ውስጥ ባሉ የአካዳሚና የሆሎታ ምሩቆች መካከል ሽኩቻ ስለፈጠረ በወቅቱ አዛዥ የነበሩት ኮሎኔል ጌታቸው ናደው ጉዳዩን ደርሰውበት መኮንኖችን በሙሉ ሰብስበው ሁኔታው እንዲቆም ያስጠነቅቃሉ። በዚህ ጊዜ 34 የአካዳሚ ምሩቃን በብርጌዱ ውስጥ ነበሩ። ሥውር ዕንቅስቃሴውና ወረቀት ብተናው ባለመቆሙ የብርጌዱ አዛዥ ለበላይ ስለአመለከቱ የክ/ጦሩም አዛዥ ጀኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ ሻምበል መንግሥቱ ኃ/ማሪያምን እንደቀጡና በግል ማህደራቸው አሳዳሚ የሚል እንዳሠፈሩ፤ በዚህም የተነሣ 19ኛ ኮርሶች ሲሾሙ ሻምበል መንግሥቱ ሳይሾሙ በመቅረታቸው  ጀኔራል ኃይሌን ሹሜቴን ያገዱና ለአካዳሚዎች የቆሙ ናቸው በማለት ከፍተኛ ጥላቻ አደረባቸው።

የየካቲት 66 ዕንቅስቃሴ ሲጀመር ሜ/ጄኔራል ኃይሌ የምድር ጦር ም/ አዛዥ፤ ሻለቃ መንግሥቱ ደግሞ የክ/ጦሩ መሣሪያ ግ/ቤት አዛዥ ነበሩ። የጦር ክፍሎች አቤቱታቸውን ለበላይ እንዲያቀርቡ ሲደረግ ከ3ኛ ክ/ጦር መምሪያ የበታች ሹሞች ዋና ጥያቄ ሆኖ የቀረበው ሜ/ ጄኔራል ኃይሌ ከምድር ጦር ም/አዛዥነት እንዲነሱ ነበር። ከዚህ ጥያቄ በስተጀርባ የሻለቃ መንግሥቱ እጅ እንደነበረበት ለማንም ግልጽ ነበር። ሻለቃ መንግሥቱ ሥልጣን ላይ እንደወጡ ሜ/ጄኔራል ኃይሌ ባይከዳኝን ከ60ዎቹ የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር እንዲገደሉ አድርገዋል። ሻለቃ ጥበበ መንክር በጊዜው በምድር ጦር መሐንዲስ መምሪያ ተመድበው ይሠሩ ነበር። መሐንዲስ አመጸ ተብሎ ተኩስ መከፈቱ ይታወሳል፡ ዓላማው ግን ሻለቃ ጥበበን በሃሰት ምስክር ይዞ ለማሰር የተሠራ ቲያትር እንደነበረ ብዙዎች ይናገራሉ። ሻለቃው ስምንት ዓመት ያላንዳች ምክንያት በእስር እንዲሰቃዩ አድርገዋል።

ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማሪያም ከልጅነታቸው ጀምሮ የበታችነት ስሜት እንደነበራቸው በቅርብ የሚያውቋቸው ይናገራሉ። መኮንን ከሆኑም በኋላ የተጠናወታቸው የበታችነት ስሜት የተነሳ በማዕረግም ሆነ በዕውቀት የሚበልጣቸውን የሚጠሉና ለማጥፋት ወደኋላ የሚሉ አልነበሩም። የደርጉ ሊቀመንበር እንደሆኑ በሠራዊቱ ውስጥ ከሻለቃ በላይ የነበሩ መኮንኖችን አድሃሪ በማለት አሰናብተዋል። በዕውቀት የሚበልጧቸውን መኮንኖች የሚያፈራውን ተቋም ለማፍረስ ጊዜና ሁኔታ ሲጠብቁ ቆይተዋል። ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ መኮንን ሆነው ሐረር

ከተመደቡ ጀምሮ የሀገር መሪ ሆነው ሥልጣን ላይ እስከወጡበት ድረስ ድርጊታቸውን ወደኋላ ሄዶ ለተከታተለ በተቋሙና በምሩቃኑ ላይ በውስጣቸው ያደገው ጥላቻ አካዳሚው ለሀገር ከሚሰጠው ጥቅም በልጦ ለአካዳሚው መዘጋት ዋነኛው ሰው መሆናቸውን ለመረዳት አያዳግትም። አካዳሚን የሚያከል ትልቅ ተቋም እንዲዘጋ የሚያዘው የአገሪቱ መሪ እንጂ ሌላ ማንም ባለሥልጣን አድርገ ካልተባለ በስተቀር አይችልም። አንድ ሰው ሲሞት ለመሞቱ ማረጋገጫ የሙት ሠርቲፊኬት (Death Ceretificate) ይጻፍለታል፤ በተመሳሳይ ለሐገር ጠቃሚ የሆኑ ትላልቅ ተቋማትን ለመዝጋት አስፈላጊ ሲሆን በሐገሪቱ መሪ በተፈረመ ደብዳቤ ወይም መሪው በወከለው ባለሥልጣን ፊርማ ታዞ ይዘጋል፤ይህም ለመዘጋቱ ሕጋዊ ማረጋገጫ ነው። አካዳሚው እንዲዘጋ ከሌ/ኮሎኔልም መንግሥቱ ኃ/ማሪያምም ሆነ ከሌላ ባለሥልጣን የተሰጠ የጽሑፍ ትዕዛዝ ባለመኖሩ አካዳሚው በሕጋዊ መንገድ መዘጋቱን ማረጋገጥ አይቻልም። አካዳሚው ተዘግቷል፤ ሞቷል ግን የሙት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት አልተሰጠውም።

አካዳሚው የተዘጋው ብልሃነትና ብልጠት በተመላበት ሁኔታ ታቅዶ የተከናወነ ነበር። የአዘጋጉ ሁኔታ ሲጤን እንደ ትልቅ ዛፍ ቆራጭ የሚከተለውን ዘዴ በሚመስል መንገድ የተከናወነ ነበር። ዛፍ ቆራጭ መጀመሪያ ቅርንጫፎቹን ተራ በተራ እየቆረጠ ዋናው ግንድ ብቻውን ሲቀር በቀላሉ ቆርጦ ይጥለዋል። በአካዳሚውም የተፈጸመው ይህንኑ በሚመስል መልኩ ነበር። የአካዳሚው የጀርባ አጥንትና የተቋሙ ተቆርቋሪ ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱትን መኮንኖች በማንሳት ልምድ የሌላቸውንና የበላይን ፍላጎት ያለምንም ጥያቄ የሚያሳኩ መኮንኖች በመተካት ቀስ በቀስ አካዳሚውን ገዝግዘው ጥለዋል።

የማንኛውም አገር መከላከያ ሠራዊት መኮንኖችን አንደኛ በጥራት ላይ ያተኮረ ሁለተኛ በብዛት ላይ ብቻ ያተኮረ የማሰልጠኛ ተቋማት አሏቸው። በሠራዊቱ ውስጥ ከሁለቱ ተቋም የተመረቁ መኮንኖች ሚዛን የተጠበቀ ነው። ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ በጥራት የሚያሠለጥነውን ተቋም ዘግተው በብዛቱ ላይ ብቻ በማተኮራቸው በኋላ ላይ በሠራዊቱ ውስጥ በአመራር ብቃት ማነስ የተፈጠረው ችግር እሳቸውን እንዲኮበልሉ ሲያደርግ አገሪቱንም አሁን የምትገኝበት ማጥ ውስጥ ከቷል።

በወቅቱ በአፍሪካ ተወዳዳሪ ያልነበረው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ ከሀገር ሕልውና ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያለው ተቋም በመሆኑ እየጎለበተና እያደገ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ ሲገባው እንዲዘጋ ተደርጓል። የሚያሳዝነው ነገር መዘጋቱ ብቻ ሳይሆን የአካዳሚው መዛግብት ሁሉ እንዲወድሙና ታሪኩ እንዲጠፋ መደረጉ ነው።የሶማሊያ ወራሪ ጦር ወደ ሐረር ከተማ ተቃርቦ ሥጋት በመፈጠሩ በአካዳሚው ውስጥ ይሠለጥኑ የነበሩ ዕጩ መኮንኖች ወደ ሆሎታ ሐምሌ 28 ቀን 1969 ዓ/ም ሲወሰዱ፤ የአካዳሚው መዛግብት ሁሉ አብረው መወሰድ አሊያም በጥንቃቄ በግምጃ ቤት መቀመጥ ሲገባቸው ተጥለው ለሐረር ከተማ ነጋዴ ዕቃ መጠቅለያነት ውለዋል። የሶማሊያ ወረራ ስጋት ከተወገደ በኋላ አካዳሚው በብ/ጄኔራል ተስፋዬ ትርፌ አዛዥነት ካድሬዎችን በዕጩ መኮንንነት ተቀብሎ በአጭር ጊዜ አሰልጥኖ አስመርቋል። አካዳሚው እንደገና የመከፈት ተስፋ አሳድሮ ነበር፤ ሆኖም ብ/ጄነራል ተስፋዬ ትርፌ አዲስ የተከፈተው የኡርሶ ማሠልጠኛ ጣቢያ አዛዥነት ተሹመው እስታፋቸውንና ለሥልጠና ጠቃሚ የሆኑ ቁሳቁሶችን ይዘው እንዲሄዱ ታዘዙ። የአካዳሚውም እንደገና የመከፈት ተስፋ አከተመ።

የአካዳሚው ደብዛ እንዲጠፋ የነበረው ፍላጎት ምን ያክል እርቀት እንደተሄደ የአካዳሚውን አርማ የያዘ ቀለበት እንዳይሠራ መከልከሉ በቂ ምስክር ነው። የአካዳሚውን ዓርማ ክልሼ ሕንድ አሠርቶ ካመጣ በኋላ በሀገር ውስጥ በጊዜው ታዋቂ ወርቅ አንጣሪ ከነበሩት ከአቶ ክብርዬ ደጀኔ ጋር አካዳሚው ኮንትራት ተፈራርሞ ክልሼውን አስረከባቸው። ከአካዳሚውና ከምሩቃኑም በሚቀርብላቸው ጥያቄ እየሠሩ ያስረክቡ ነበር፤ ነገር ግን አካዳሚው እንደተዘጋ አቶ ክብርዬ ደጀኔ ክልሼው ጠፋብኝ በማለት መሥራትም ሆነ መሸጥ አቁመዋል። ይህም አካዳሚው እንዲዘጋና ታሪኩ እንዲጠፋ ባደረጉ ባለሥልጣኖች በተሰጠ ትዕዛዝ ነው የሚል ግምት አለ። ስለዚሁ ጉዳይ አቶ ክብርዬ ደጀኔን በቅርብ የሚያውቃቸው አንድ የአካዳሚ ምሩቅ (ሌ/ኮሎኔል ፋንታሁን ተምትሜ) አነጋግሯቸው ክልሸው በአያያዝ ጉድለት እንዳልጠፋ ጠቅሰው፤ ጠፋ የተባለበትን ምክንያት ግን ሳይጠቁሙ እንደ ጥላሁን ገሠሠ ሆድ ይፍጀው በማለት ምሥጢሩን ይዘውት ወደ መቃብር ወርደዋል።

ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያም በተቋሙና በምሩቃኑ ላይ በነበራቸው ጥላቻ አካዳሚውን አዘግተዋል፤ የተለያየ ምክንያት በመስጠት 54 የአካዳሚው ምሩቃን መኮንኖችን አስረሸነዋል፤ በአካዳሚ መኮንኖች ላይ እምነት ሳይጥሉ ከሥልጣን ለመባረር በቀተቃል። የአገር መሪ በራሱ ስሜት ብቻ ተነሳስቶ ነገ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ሳያጤን ዛሬ የሚወስደው እርምጃ ነገ በተተኪው ትውልድና በአገር ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ችግር፤ የሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማሪያም ድርጊት ለአሁኑ ትውልድ አስተማሪ ይመስለኛል

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ በጥላቻ ተወልዶ፤ በጥላቻ ውስጥ ኖሮ፤ በጥላቻ ተገሎ የመሞቱ ማስረጃ (Death Ceritificate) እንኳ ሳይኖረው ቢቀበርም ያፈራቸው ጀግኖች ታሪክ ውስጥ አካዳሚውም ስለሚወሳ ሕያው ሆኖ ይኖራል።

GC 656